★ዴሞክራሲያ★

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞክራሲያ ቅፅ 40 ቁ. 1 ጥቅምት 2007 ዓ.ም.

# ጭቆናን ማሰንበቻ ወይስ ነጻና ፍትሓዊ ምርጫ?

ቀደም ብሎም ሆነ በተለይም ባለፉት 23 አመታት ውስጥ ኢሕአፓ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫን በሚመለከት በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በሀገራችን ተጨባጭ ሁናቴ ተግባራዊ ሲሆን ምን መልክና ይዘት እንዳለው፣ ለተግባራዊነቱም በቅድሚያ ተሟልተው መገኘት ስለሚኖርባቸው ዝርዝር ጉዳዮች፣ በተለያዩ ጊዜያት ስፋትና ጥልቀት ያላቸውን ትንታኔዎች በዴሞክራሲያ፣ በፍኖተ ዴሞክራሲ የሬዲዮ ስርጭቶች፣ በፓርቲው መግለጫዎች፣ በተሰጡ ቃለ መጠይቆች ግልፅ ተደርገዋል። የተደረጉት ጥረቶች የሕዝባችንን ንቃተ-ሕሊና ያሳደጉና ሰፊ ግንዛቤን እንዳስጨበጡ ይታመናል።

በመሆኑም በሀገራችን ተከስተው ያሉ ችግሮች በዘላቂነት የሚወገዱበት ሥርዓት በሕዝቡ ትግል እስካልተመሰረተና የአምባገነንን እድሜ የሚያራዝሙ፤ የይስሙላና የተጭበረበሩ የምርጫ ትያትሮች ወቅቶች እየተጠበቁ ተግባራዊ የሚሆኑበት ጥረቶች እስካላከተሙ ድረስ ኢሕአፓ ስለ ነፃ፣ ርቱዕና ፍትሃዊ ምርጫ ያለውን ግንዛቤና እይታ ከወቅቱ ሁናቴ ጋር በማያያዝ ሳይታክት ለሕዝብ እየደጋገመ ማቅረብ የሚጠበቅበትና አግባብነትም ያለው ነው። ኃላፊነቱና ግዴታውም ነው። በአሁኑ ወቅትም በዚህ ዓመት ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቀው የምርጫ ተውኔት ለሕዝብ የሚፈይደው ነገር እንደማይኖር ግልጽ ሆኖ ሳለ ያንኑ የለመድነውን ለመድገም ወያኔ እየተሯሯጠ መሆኑ በገሃድ ይታያልና፤ የማወናበጃ ዘዴዎችንም ቀጥሎበታልና በበኩላችን ምን መደረግ እንዳለበት፤ የትግላችን ዓላማ ምን መሆን እንደሚኖርበት ፤ አቅጣጫውንም ሆነ ሂደቱን በዝርዝር የማስረዳት ኃላፊነትን በተገቢው መወጣት የዜግነት ግዴታ መሆኑን አጥብቀን እንገነዘባለን። ይህንን ኃላፊነት ለሚቀጥለው ትውልድ የሚያስተላልፉት አይደለምና በርዕሱ ዙሪያ በአገዛዙም ሆነ በሌሎች እየተነዙ ያሉትን የተሳሳቱ አመለካከቶችን ማረምና እየተገበሩ ያሉ የማወናበጃ ዘዴዎችንም ማጋለጥ ተገቢ እርምጃ ነውና ይኸው ትንተናችንን እናቀርባለን።

በኢሕአፓ እይታ አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገኝበት ተጨባጭ ሁናቴ የትግሉ ዓላማና ግብ መሆን የሚገባው ውጤቱ አስቀድሞ ለሚታወቅ ተውኔት አጃቢ በመሆን የዘረኛ አገዛዝ እንዲቀጥል አስተዋፅዖ ማበርከት ሳይሆን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱ እንዲረጋገጥ፤ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን ፤ የሀገር ነፃነትና ሉአላዊነት፤ የዜጎች እኩልነት፤ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩባቸው ሥርዓት ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ካለፉት ጊዜያት በበለጠ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ

ከመንቀሳቀሱ ላይ እንደሆነ ከፍተኛ አፅንዖት እየሰጡ መግለፁ ተገቢ ነው። ይህ መሰረታዊ ሃሳብ አጽንዖት ተሰጥቶበትም የሚገለፀው ደግሞ ያለምክንያት አይደለም።

ላለፉት 23 አመታት ሕዝባችንን እንደማነቆ ይዘዉት የነበሩትና አሁንም ያሉት ችግሮቹ ቀጣይ ሊሆኑ የቻሉት ወያኔ የራሱን ድርጅታዊ ፕሮግራም እንደ ሀገሪቱ የመተዳደሪያ ሕግ አድርጎ በሕዝባችን ጫንቃ ላይ በግዴታ በመጫን፣ በዘረኝነት የተቃኘ የፖለቲካ ፕሮግራሙን ሕጋዊ መሠረት ሰጥቶ ለመተግበር በመቻሉ እንደሆነ ከወያኔና እፍኝ ከማይሞሉ ደጋፊዎቹ በስተቀር ብዙሃኑ ዜጎቻችን የሚስማሙበት ነው። በብዙሃኑ እምነትም የሕዝባችን መሰረታዊ ችግሮች ወያኔ በመጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳው እንደሚነዛው መፍትሄ አግኝተው የተወገዱ ሳይሆኑ፣ ይበልጡኑ እየተባባሱ መሄዳቸው በቀን ተቀን መራራና አሰቃቂ ኑሯቸው የሚገለጽ እንደሆነ በራሳቸው አንደበት በተለያዩ ጊዜያት ከገለጿቸው ሀቆች የበለጠ ዋቢ አይገኝም። ስለሆነም ዜጎቻችን ሙብት አልባ ኑሮን ለመኖር እየተገደዱ ባሉበት ሁኔታ በሚነዛላቸው መጠነ ሰፊ የእድገት ፕሮፓጋንዳ ብሩህ ተስፋ አልታይ ቢላቸው አይፈረድባቸውም። ከሙብት ጥሰቶችና በደሎች ባሻገር ወሳኝ የሆኑ የውሃ፡ የኤሌክትሪክ ኃይል፡ የስልክ፡ የመጓጓዣ የመሳሰሉ የአገልግሎት አቅርቦት በሚያሳዝን ሁናቴ ለብዙሃኑ አለመዳረስ፤ ለጥቂቶቹም ቢሆን መስተጓጎልና ሕዝብ አቤት የሚልበት መታጣት፤ በከፍተኛ ደረጃ የሙስና ተግባራት መንሰራፋት፤ በርካታ ዜጎቻችን በከፋ ድህነትና በቀላሉ ሊወገዱ በሚችሉ በሽታዎች እንኳ መሰቃየትና መንገላታት፤ በፍትህ እጦት የሚደርሱት በደሎች ሕዝብን ማማረሩና በወያኔ አገዛዝ ላይ ጥላቻ ማሳደራቸው ከብዙዎቹ በጥቂቶቹ የሚጠቀሱ ናቸው።

ስለሆነም ለነዚህና ሌሎች በርካታ ችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ከትከሻቸው ላይ ተቆናጦ የሚገኘውን ከይሲና ጎጠኛ ኃይልን ከማስወገድ ሌላ አማራጭ የለም። ከተለያዩ ተመክሮዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው ወያኔ በሕዝባዊ ትግል ካልተገደደ በስተቀር ስልጣን የሚለቅ አይደለም። ምክንያቱም በለስ ቀንቶት የግል አጀንዳውን ተግባራዊ ለማድረግ የቻለበትን የፖለቲካ ምህዳር በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ አማካኝነት ራሱን የሚያስወግድበትን ሁናቴ ለማመቻቸት ሀሳቡም ፍላጎቱም ስለሌለው ነው። በሥልጣን ላይ ለመቆየት ያለው ሱስና ለሕዝብ ፍላጎት ተገዢ ላለመሆን ያደረበት ትእቢት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ለመሄዱ ከጉያው የሚወጡት የጓዳ ውሳኔዎቹ የሚንፀባረቁት ነው። ስለሆነም በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ሁናቴ እንዲቀጥል መፍቀድ በሕዝብ ላይ ያስከተሉትን ከፍተኛ ጉዳቶች፡ በሀገርና በሕዝብ አንድነት ላይ ያደረሱትን ጠንቆች አይቶ አለማየት ብቻ ሳይሆን በሕዝብ ቁስል ላይ የደረቀ እንጨት ከመሰንቀር ውጪ የማይታይና በበኩላችን በጥብቅ ሊወገዝ የሚገባው እንደሆነ የፀና እምነታችን ነው።

ተደጋግሞ እንደተገለፀው በኢትዮጵያ-ረጅም ታሪክ ብዙሃኑ የሆኑት ግፉአን ለዘመናት የታገሉለትን የሕዝብ ልዕልና እስከዛሬ ባለመቀዳጀታቸው የራሳቸው ታሪክ ገና አልተጻፈም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በገዛ ፈቃዱና ድምፁ የሰየመው መንግሥትና በሕዝብ ይሁንታን ያገኘ ሕገ-መንግሥት ያልነበረና ዛሬም የሌለ ስለሆነ ሁለገብ ሙብቱም ይሁን ሀገራዊ አንድነቱና ፍላጎቶቹ ሊከበሩለት አልቻሉም። በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የከፈለው መስዋእትነት እጅግ ከባድና መራራ ቢሆንም ዘላቂነት ያለው ሠላም አግኝቶ ሉዓላዊነቱ በማይናጋ መሠረት ላይ ባረፈ ሕገ-መንግሥታዊና ዴሞክራሲያዊ ሙብቶች የተከበሩባት ሀገር ውስጥ ታፍሮና ተከብሮ እፎይ ብሎ ለመኖር አልቻለም።

የፋሽስታዊው የደርግ አገዛዝ መውደቅና በጎጠኛው የወያኔ ቡድን መተካት ይህንን ሐቅ የሚሽር ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህም ዛሬም የአገራችንን ሁኔታ ከወዲሁ ሆነው ቢያዩት ያው የበፊቱ፣ ከወዲያም ሆነው ቢያማትሩት እዚያው እነበረበት ሥፈራ ላይ ከመቸንከሩም በላይ እንዲያውም በብዙ ገፅታዎቹ እየተባባሱ ስለመጡ ነገሩ ሁሉ ከድጡ ወደ ማጡ ከመሆን የሚያልፍ

አልሆነም። በማንኛውም ጊዜና ቦታ እንደታየው የመንግሥት ሥልጣንን በሕዝብ ይሁንታና ፈቃድ ያላገኙ አምባገነኖች ጠብ-መንጃን መከታ በማድረግ በሚገዙት ሕዝብ ላይ የትልቅነት ማንፀባረቂያ፣ የቂም በቀል መወጣጪያ፣ በውስጣቸው ያለውንም ቅራኔና ጥላቻ መፍቻ አድርገው በመጠቀም የግፍ አገዛዛቸው እድሜና የብዙሃኑን ህዝብ የስቃይ ዘመን ለማራዘም ሲጠቀሙበት የታየ ለመሆኑ ሕዝብ በተደጋጋሚ የተገነዘበው ሐቅ ነው።

ከዚህ አጠቃላይ ግንዛቤ ስንነሳ ዛሬ በአገራችንና በሕዝባቸን ላይ የተጫነው ወያኔያዊ ዘረኛ አገዛዝ እንደማንኛውም አምባገነን ሁሉ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጥላቻና ለሕግ የበላይነት ፍርሀት ስላለው በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ምርጫና የዴሞክራሲ ጽንሰ-ሀሳብ እንዳያቆጠቁጥና እንዳይስፋፋ፤ የአሰራር ዘዴው ሥር እንዳይሰድ፤ ባህሉ እንዳይለመድ፤ የማይቧጥጠው ዳገት፤ የማይፈነቅለው ድንጋይ እንደሌለ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመስከረው ገሀድ ከሆነ እነሆ 23 ድፍን አመታት አለፈው።

ዛሬም ወያኔ እንደቀደሞው፤ እንደጫካ ህይወቱ ፤ መጽሐፈ ወያኔን የተቃወመ ጥፋተኛ ወይንም ወንጀለኛ ነው። የወያኔ መሪዎች በአጉል እብሪት ተቀይድው የሠላምና የዴሞክራሲ አማራጭ (ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ) አይታያቸውም። በመሆኑም ወያኔዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ነጻና ፍትሀዊ፤ የዴሞክራሲያዊ ምርጫን መሥፈርቶች ያነሳ ሁሉ ጸረ-ልማት፤ ሽብርተኛና ወንጀለኛ የሚል ተቀጽላ እየተሰጠው ዘብጥያ ይወርዳል። ወያኔዎች ሕዝቡ ለየት ያለ ሀሳብ ሲያነሳ፤ ቅሬታውን ሲገልጥ፤ ተቃውሞውን ሲያሰማ ያስደነግጣቸዋል። ቅሬታን መግለጥ፤ ተቃውሞን ማሰማት፤ የተለየ ሀሳብን ማቅረብ፤ በነጻነት መደራጀትና፤ የመሰለውን መምረጥ የሕዝቡ መሠረታዊና፤ የማይገረሰሱ ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ መሆናቸውን ለማስመሰያ ካልሆነ በስተቀር ተግባራዊ ሊያደርጉ አይቃጣቸውም፣ ፍላጎቱም የላቸውም። ወያኔ ከውልደቱ ጀመሮ ሁሌም ጥረቱ በኃይል እኩይ ተግባሩን ለመፈፀም እንጂ በሠላምና በዲሞክራሲ ዙሪያ ለሕዝቡ ጥያቄ መልስ ለመስጠትም ሆነ መፍትሄ ለማግኘት አልነበረም አሁንም አይደለም። ወያኔ የሚመራበት መርህ ከደቀ መምህራኖቹ እንደተሰጠው ትምህርት "ዴሞክራሲያዊ ማስመሰል፤ ነገር ግን ሁሉንም በኛ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ማድረግ" በሚለው እየተንቀሳቀስ ያለ አምባገነን ቡድን ነው።

ለዚህም ነው እኛ ለዴሞክራሲ፤ ለነፃና ፍትሃዊ ምርጫ፤ ለሀገሪቱ ሉዓላዊነት መረጋገጥ፤ ወያኔ ለምን አልቆመም? ብለን አንጠይቅም ። ብለን ነበር ማለቱ ለዛሬው ችግር መፍትሔነት አይኑረው እንጂ ወያኔ ከውልደቱ ጀምሮ ፀረ-ዲሞክራሲ መሆኑን ተናግረናል። ዛሬም ወያኔ ፀረ- ሕዝብና ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይል መሆኑን የሚገልፁ በርካታ ማስረጃዎችን ማስታወስና መግለፅ ይቻላል። ወያኔ መቼም ቢሆን ለፍትህና ለዴሞክራሲ ቆሞ አያውቅም ስንል በዘፈቀደ ወይም በጭፍን ጥላቻ ሳይሆን የድርጅቱን የ41 ዓመት ተግባሩን፤ ባህሪውንና የእንቅስቃሴ ታሪኮቹን በመገምገም ግንዛቤ በማግኘታችንና የጫካውንም ሆነ በባዕዳን ድጋፍ ሥልጣን ላይ ለመቆናጠጥ የቻለውን ተቆናጦ ያለውን ወያኔ ጠንቅቀን የምናውቅ በመሆናችንም ጭምር ነው።

ባለፉት ጊዜያት በተደጋጋሚ እንደገለፅነው በደንብ መጠየቅና መመርመር ያለበት ጉዳይ ወያኔም ሆነ ተመሳሳይ ባህሪይ ያላቸው አምባገነኖች ለምን ሕዝባዊና ፍትህዊ ምርጫን ይፈሩታል የሚለውን መሠረታዊና ዓቢይ ጥያቄ ነው። በኛ እምነት መልሱም አጭርና ግልጥ ነው። ሁለቱም ከሕዝብ የተነጠሉ፤ ፀረ-ዲሞክራሲና በሕዝብ ላይ የታበዩ በመሆናችው ነው። ወያኔ የሕዝብን መብትና ህልውና ረግጦ እየገዛ በመሆኑ ከእያንዳንዱ የኅብረተሰብ ክፍል የተነጠለና የተገለለ ከመሆኑም ባሻገር በየጊዜው እያደገና እየጎለበተ ባለው ሕዝባዊ ትግል(አመፅ) ጭምር እየተፈተነ ያለ አምባገነንና አናሳ ቡድን ነው። ወያኔ በቅራኔና በውጥረት ውስጥ መገኘቱ ግልጽ ነው። በቀን ሶስት ጊዜ ጠግቦ እንደሚመግብ ሲደስኮርለትና ሲሰበክ የቆየው የኢትዮጵያ

*ሕዝብ ዛሬ ከትናንቱ በባሰ የኢኮኖሚያዊ ችግር ውስጥ ሲዘፈቅ፤ ተስፋው እየሟሸሸም ሲመጣ፤ ያተረፈው ነገር ኢ-ፍትሀዊነትን፤ የከፋ ድህነትና ችግርን ሲሆን ለዚህ ባበቃው አገዛዝ ላይ ያመረረ ተቃውሞ በተለያዩ አካባቢዎችና ዘዴዎች ማድረጉ ስጋት እንደፈጠረበት መገንዘብ አዳጋች አይደለም።*

*ወያኔ ከዚህ ወጥሮ ከያዘው ሕዝባዊ አመፅ ወደፊትም ስፋትና ጥልቀት እያገኘ ከሚሄደው ሕዝባዊ ተቃውሞ ለማዘናጋት የሕዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳት "ባንዲራህ ተደፈረ!" "ሽብርተኞች ልማትህን ሊያደናቅፋብህ ነው!" ታላቁ የህዳሴውን ግድብ ሊያፈርሱብህ ነው!" ... ወዘተ በሚል የአምባገነኖች ፈሊጥ መጪውን የወያኔ የምርጫ ቧልት እንደተለመደው ለብቻው ተወዳድሮ በምርጫ አሸነፈኩ ለማለት ሕዝቡን ለማዘናጋት መጣሩ ሳይታለም የተፈታ ለመሆኑ የፅንሰ ሃሳብ መጽሐፎች መግለጥም ሆነ የባዕዳን ተመክሮዎችንም መዘርዘር አያሻንም።*

*ወያኔ ምርጫ በመጣ ቁጥር አስመሳይ ተውኔቶችን በየፈርጃቸው ይፈበርካል። ሥልጣን ከጨበጠ ጀምሮ አምርሮ የሚጠላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመሸንገል ለመደለልና ደጋፊ ለማድረግ ይሞክራል። የወያኔው አሻንጉሊት ፕሬዜዳንት ተብየውም የ2007 የፓርላማ መክፈቻ ንግግሩ ይህንኑ የተለመደ የወያኔ ድራማ አመላካች ነው። ይህንን መሰሉን ሁኔታ በመጠቀም ለዴሞክራሲና ለእኩልነት፣ ለሀገሩ አንድነት የሚታገለውን ክፍል ከሕዝብ ለመነጠልና ለማዳከም ጥረት እያደረገ መሆኑ የሚታይ ነው። ከዴሞክራሲያዊና ሕዘባዊ ኃይሎች ጎን ተደራጅተው ሊሰለፉ ሕዘባዊ ትግሉንም ሊቀላቀሉ ይችላሉ ብሎ የሚገምታቸውን ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ የሆኑ ኃይሎችን በተለይም አጥብቆ የሚፈራውን፤ ለውጥ ፈላጊውን ወጣቱን ትውልድ በተለያዩ ጥቃቅን ጥቅማ ጥቅሞች ለመደለልና ለወያኔያዊ የግፍ አገዛዙ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ፤ ሽብርና ፍርሃትን ጠዋት ማታ የኢትዮጵያ ሕዘብ አንጡራ ኃብት በሆኑት የብዙሃን መገናኛዎች አማካኝነት የጥላቻ ፕሮፓጋንዳውን እያሰራጨ ይገኛል።*

*ስለ ሕዝባዊ ምርጫ ስናወጋ መሰረት የሚሆኑን ምንም እንኳ በአጼውና ደርግ አገዛዝ ዘመን የተገኙ ተመክሮዎች እንዳሉ ሆነው በወያኔ አገዛዝ ዋና አቀናባሪነት የተካሄዱት አራቱ ምርጫዎች በራሳቸው ሕዝባችን የተሳተፈባቸውና በቂ ተመክሮንም የጨበጠባቸው ናቸውና የውይይት መሰረቶቻችን መሆናቸው የግዴታ ነው። እስካሁን በወያኔ ሥር የተካሄዱትን ምርጫዎች ስንገመግም አንዱ ከሌላው የሚለይበት መሥፈርት ቢኖር በምርጫ ሥም የሚጠፋው የንጹሐን ሕዝብ ህይወትና የሚወድመው የሕዝብ ንብረት መጠኑ እያደጉ መሆናቸው ነው። ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው ዛሬም አገራችን ፍትህና ዲሞክራሲ የሰፈነባት፡ የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት የተረጋገጣባት ሀገር ለመሆን አልታደለችም። በሀገራችን መንግሥት ማለት በሕዝብ ላይ የተጫነ የሥልጣን ልጓምን ጨብጦ እንዳሻው የሚፈልጥና የሚቆርጥ ፤ ከህዝብ ተነጥሎ የቆመ፡ የማይደፈር፡ የማይገረሰስ ኃይል ወይም ፍጡር ሆኖ ቆይቷል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋናውና መሠረታዊው ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው የህዝብን ይሁንታ ያገኘ ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሕዝባዊ መንግሥት አለመምሥረቱና አገርና ህዝብ የሚተዳደሩበት ዴሞክራሲያዊ ህገ- መንግሥት በሕዝብ ይሁንታ ፈቃድ አለመኖሩ ጭምር ነው።*

*ስለሆነም ወያኔ በያዝነው 2007 ዓ.ም. ይካሄዳል ተብሎ ስለሚጠበቀው የምርጫ ቲያትር ቀደም ባሉም ጊዜያት ወያኔም ራሱም ቢሆን ከደረሰበት ሽንፈት ተመክሮን የቀሰመ በመሆኑ ከወዲሁ ያው እንደተለመደው ራሱ በራሱ ተወዳድሮ በአሸናፊነት የሚወጣበትን ቀመር በሚገባ ለማዘጋጀቱ ላለፉት ሁለት አመታት ያደረጋቸው ድርጊቶቹና አሁንም ድረስ በቀጣይነት የምንመለከታቸው እንቅስቃሴዎቹ የሚመሰክሩበት ናቸው። በኮሚኒኬሽን ሚኒስትሩ የበላይነት በጥቅምት ወር የተደረገው የምርጫ ዘመቻ ዝግጅት በወያኔ አሸናፊነት የተቃኘው ሴራም ሆነ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተሰጠው ምርጫ*

ተኮር ሥልጠናም ለምሳሌ የዚሁ አካል ናቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ነጋ ጠባ የሚለፈልፈው የአገዛዙ ሥርዓት "ትክክለኛ" በመሆኑ መቀጠል አለበት የሚለው ልፈፋው ከሱ በስተቀር ተቀባይነት የማጣቱ ጉዳይ እያስደነገጠው መገኘቱም እየታዘብን እንገኛለን። የፌደራልና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ሀገር አቀፍ ጉባዔ ተደርጎ በምርጫና በዳኝነት መዋቅሩ መካከል የጠበቀ ቁርኝት እንዲኖር የተወሰነበት ስብሰባ የሚያመላክተውም ይህንኑ ነው።

የዴሞክራሲያዊ ባህልና የዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ሥርዓት አለመኖር ወይ አለመዳበር በአንድ መንግሥታዊ ይዞታ አንፃር የሚመረመር ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ነው። ዴሞክራሲያዊና ፍትሀዊ ምርጫ ስንል ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት የሚያደርግ በተቃራኒው ደግሞ አምባገነኖች በተጭበረበሩና የማስመሰያ ተውኔቶች ከሥልጣን እንዳይቆናጠጡ የሚከላከል የፖለቲካ እሳቤ ማለታችን ነው። ዲሞክራሲና የዲሞክራሲያዊ ባህል ሕዝቡን እንደወሳኝ ኃይል የመቀበል እምነት፤ አመለካከትና፤ ክንዋኔና በዚህ ላይ የተመሰረተ የመንግሥት አወቃቀር ወይም መዋቅር መዳበሩን የሚያመለክት ማለት ነው። ነፃ ምርጫ ስንል በቅድሚያ የሕዝቡን የመብት መረጋገጥን ያጠቃልላል።

ኢትዮጵያዊ መንግሥት ስንል የተለያየ ትርጉም ሊሰጠን የሚገባው አይደለም። እኛ ኢትዮጵያዊ መንግሥት ስንል ከነፃና ፍትሐዊ ምርጫ የሕዝብ ይሁንታን አግኝቶ ''ተቀመጥ በወንበሬ፤ ተናገር በከንፈሬ'' ተብሎ የብዙኑን ይሁንታ/ድጋፍና ድምጽ/ ያገኘ ማለታችን ነው። የሕዝብ መንግሥት ስንል የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም፤ አንድነት፤ ሉዓላዊነትና ሥልጣነ-መንግሥት አክብሮና አስከብሮ ለማቆየት ግዴታውና መብቱ አድርጎ የሚያይ ማለት ነው። በዓለም አቀፍ መድረኮች ውስጥ የኢትዮጵያን ጥቅም በቀዳሚ ግብነት--አጀንዳነት የያዘ፤ ለዚህም ጥቅም ማስከበሪያ ከሕዝብ አብራክ የወጣ የአገርን ዳር ድንበርና ሥልጣነ መንግሥት የሚጠብቅና የሚያስጠብቅ ነው። ዜጎችን ሁሉ በአንድ ዓይን የሚያይና የወልና የግል ሕዝባዊ መብትን የሚያከብር ነው። የሕዝብ ይሁንታን ያገኘ መንግሥት ለኃላፊነት ወደ ሥልጣን የሚጠራቸው ሰዎችም በችሎታቸው እንጂ ዛሬ በስፋት ተግባራዊ ተደርጎ እንደሚታየው በዘር፤ በሃይማኖትና በመንደር ልጅነት መሆን የለባቸውም።

ዛሬም እንድትናንቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገሩ የፖለቲካ አካሄድ በመንግሥት ተዓማኒነትና ሐቀኝነት ተስፋ በመቁረጥ የመልካም አስተዳደር ያለህ ሲል ዘመናትን አስቆጥሯል። በእርግጠኝነት ዛሬ ኢትዮጵያችን መንግሥት አልባ ነች። አሁን ባለንበት ወቅት ኢትዮጵያ መንግሥት አላት ብሎ ኢትዮጵያዊነትን ትርጉም አልባ ማድረግ አግባብ አይሆንም። ለምን ቢባል ዛሬ በሀገራችን ሀገራዊ መንግስት የለምና ነው መልሱ ። ወያኔ ዴሞክራሲን በአፍጢሙ ደፍቶ፤ ሕዘባዊና ፍትሃዊ ምርጫን የውሀ ሽታ አድርጎ፤ ታሪክን ከዶ፤ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በታትኖ፤ ቅርሷን አዘርፎ፤ ሀገሪቷን ለባእዳን መፈንጫ እንድትሆን አድርጎ እንዴት የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ መንግሥት ከቶ ሊሆን ይችላል?። ወያኔ ገና ከጥንስሱ ከአመሠራረቱ በኢትዮጵያና ሕዝቧ ላይ ዘምቷል፡፡ የአገሪቷንና የሕዝቧን ታሪክ ጥላሸት ቀብቷል፡ መቻቻልን ለማደብዘዝ ሰርቷል፤ ሀብቷን ዘርፏል፡ በተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል ላይ የጥላቻ ዘመቻ ማካሄድ ብቻ ሳይሆን ከቄያቸው፣ እትብታቸው ከተቀበረበትና ሰላማዊ ኑሮ ከሚኖሩበት አካባቢ በማፈናቀል ለሞት፣ ለከፋ ድኽነትና ስቃይ ዳርጓል። እንዴትስ የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ የኢትዮጵያ መንግሥት ብሎ መጥራት ይቻላል? መቼም አይቻልም ነው መልሱ ።

በመሆኑም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባልሰፈነበት፤ የሕዝብ መብት ባልተከበረበት፤ ዜጎቻችን ነፃነታቸውን ባለተጎናፀፉበት ሀገር ስለ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ማውጋት በርግጥም ቀልድ ነው የሚሆነው። ይህንን ከግምት በማስገባትና ከበርካታ ተመክሮዎች ካገኛቸው ትምህርቶች ጋርም በማጣመር ኢሕአፓ ዜጎቻችን የአምባገነን ፕሮፓጋንዳ ሰላባ እንዳይሆኑ ሁሌም ማስተማር፤ ማሳወቅ፤ ማስረዳትና ግልፅ ማድረግ ተግባሩ የሚሆነውም አንዱ ምክንያት ይኸው ነው። ለዚህም ነው ኢሕአፓ

ዛሬም እንደቀድሞው የነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ቅድመ ሁናቴዎች እንዲሟሉ የወያኔ የብቸኛ ባለሥልጣን መሆን እንዲያከትም ትግሉን በፅናት እያካሄደ የሚገኘው። በኢሕአፓ እምነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባልሰፈነበትና የዜጎች መብት ባልተከበረበት ሁናቴ አሁንም እንደቀድሞው በወያኔ የበላይነት በዚህ አመት ይደረጋል ተብሎ የሚታሰበው ሕዝባዊ ምርጫ የነፃና የፍትህ ካባ ሊላበስ ጨርሶ አይቻለውም በማለት እየገለፀ የሚገኘው።

ማንም ቅን አሳቢ ለመታዘብ እንደሚችለው ይህ በ 2007 ዓ.ም. ይካሄዳል ተብሎ ስለሚታሰበው ምርጫ ተብዬ ተውኔት የወያኔ አገዛዝ ያው በተለመደው ያለፉትንና ከዚህ ቀደም ያየናቸውን ኩነቶችን ዘንድሮም ተግባራዊ ለማደረግ ዝግጅቱን ከማወናበድ ተግባሩ ጋር በማዋሃድ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ለኛም ሆነ ለሕዝባችን የተሰወረ አይደለም። ወያኔ የፖለቲካ ምህዳሩን በራሱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ባደረገበት ውስጥ እጅግ ብርቱ ተፎካካሪ ሆኖ ለመቅረብ መዘጋጀቱን ከወዲሁ እየገለፀ ይገኛል። ሰፊ ሕዝባዊ መሰረት አለኝ ሲልም ተደምጧል። የሕዝቡን የኑሮ ሁናቴ ወደተሻለ ደረጃ ማሸጋገር የሚያስችል ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማ ነኝ ሲልም በውሸት አሃዞች በማስደገፍ በማጠየቂያነት ማቅረቡ እየተሰማም ይገኛል። ለዚህም ሕዝብን ሳይሆን ባዕዳን ደጋፊዎቹን በዋቢነት ማቅረቡም በተደጋጋሚ እየተሰዋለ ነው። ይህን በገለፀበት አንደበቱም የተፎካካሪዎቹ አቅም፣ አደረጃጀትና አቋም በነፃና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ መንቀሳቀስ የሚያስችላቸው እንዳልሆኑ በራሱ ለራሱ በመመስከር "የአሸናፊነት" ድንፋታውን አስተጋብቷል። ወያኔ ሲሻው እንደ ፖለቲካ ተወዳዳሪና ድርጅት ሲፈልግ ደግሞ እንደ መንግሥት የምርጫ አስፈፃሚ በሆኑ የሁሉ ሳይሆኑ የራሱ (ልብ አድርጉ) መዋቅሮቹ በኩል ስለ ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊነት እየሰራሁ ነኝ እያለ ቢለፍፍም ይህንንም በመጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ለማስደገፍ ቢጥርም የሚያምነው እንደሌለ የራሱ መሰሪ ድርጊቶቹ የሚመሰክሩበት ናቸው።

በከፉ አይን የሚያያቸውን ቀርቶ የራሱን ሕገ አገዛዝ እያከበሩ በመንቀሳቀስ ተፎካካሪ ለመሆን የሚጥሩ ተቃዋሚ ነን ባይ ድርጅቶችን አባሎቻቸውን እያሰረ፣ እንቅስቃሴዎቻቸውን በሆነ ባልሆነው እያደናቀፈ፣ ከሕዝብ ጋር እንዳይገናኙም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ከመከልከል አንስቶ አማራጭ ፖሊሲዎቻቸውን በሕዝባዊ መገናኛ መድረኮች እንዳያሰራጩ እያገደ፣ ለአጃቢነት ሚና እንኳን የሚራራላቸው አልሆነም። በውሸት ላይ በተመሰረተ ፕሮፓጋንዳውም ሆነ በከይሲ ድርጊቶቹ ብቻ የማይተማመን ከፉኛ ተጠራጣሪ ቡድን ነውና እንደ ሥስ ስልቻ የተነፉ ፊኛዬን ሊያስተነፍሱ ይችላሉ የሚላቸውን የፀጥታ ኃይሎች ሳይቀር አፈንግጠው ከራሱ ቁጥጥር ውጭ እንዳይሆኑበት በታማኝ ሰላዮች አማካኝነት በአይነቁራኛ የሚከታተላቸው ለመሆኑ የተለያዩ ውስጣዊ መረጃዎች የሚያመላክቱ ናቸው።

የወያኔን ሕገ አገዛዝ ተቀብለው እንንቀሳቀሳለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶችም ቢሆኑ በበኩላቸው ካለፉት ምርጫዎች በትግል በደም ከተገኙ ተመክሮ ትምህርት ባለመቅሰምና በጥልቀት ባለመመልከት እያቅማሙ መሆናቸው ከሚሰጡት መግለጫዎቻቸውለመገንዘብ የሚቻል ነው። አሁንም "የፖለቲካ ምህዳሩ የጠበበ ነውና ይስተካከልን" በማለት ለችግሩ ዋና ተጠያቂ የሆነውን አገዛዝ መማፀን መቀጠላቸው በርካታዎችን ማስገረሙ አልቀረም። የተወሰኑቱ ደግሞ ቀድሞውኑ ወያኔን የሁሉ ፈጣሪና አድራጊ አድርገው በማየታቸው ችግር ሲመጣባቸው ቆርጠው ወያኔን በተገቢው ሁናቴ መጋፈጥ ከብዷቸው ተከታዮቻቸውን ለአውሬ ሲሳይ ጥለው የወጡ አሁንም ድረስ በወያኔ ላይ አንጀታቸው ያልቆረጠና ለሱ የሚሳሳ ልባ ያላቸው ቡድኖችም እየተፈጣጠሩ ከባዕዳን ሀገርም የወያኔን ምርጫ ለማጀብ ጓዛቸውን ጠቅልለው የገቡ በመጡበት እንዲመለሱ መደረጋቸው እንወክለዋለን የሚሉትን የሕብረተሰብ ክፍል ምንኛ ዳግም እንዳሳፈሩ አለመረዳታቸው ከትዝብት ጥሏቸዋል። ቀድሞውኑ የእንቅስቃሴያቸው ግብ የሥልጣን ፍርፋሪ ለመቀራመት እንጂ ነፃነትን ለማጎናፀፍ እንዳልሆነ

መረዳት ለሚፈልግ ማንኛውም ዜጋ ከዚህ የበለጠ ጉልህ ምሳሌ ሊያገኝ አይችልም። እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው እንደሚባለውም ወያኔ እንደተለመደው የፖለቲካ ምህዳሩን በራሱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር አድርጎ በምርጫ ሰሌዳ ላይ ለመወያየት ለይስሙላ ጋብዞ ከአጥር እንዳይዘሉ በመቆጣጠሪያው ክብ ሊያስገባ እየጣረ መሆኑም እየታየ ነው። በጓዶቻችን ሬሳ ላይ የተረማመዱ የኢሕአፓ ርዝራዦችም ቢሆኑ ገብተው ከጫማው ሥር ተጎንብሰው ለመነጠፍ ከደጅ ደጅ ቢያሰፈስፉለትም ጠቀሜታቸውና ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታው የማይበቁለት መሆናቸውን በመገንዘቡ ፊቱን የነሳቸው እንደሆነም የውስጥ ለውስጥ ሽኩታዎች የሚጠቁሙት ናቸው። እነዚህና ሌሎች መሰል እንቅስቃሴዎች የወያኔን ልብ እያሳበጡ ትዕቢተኝነቱንም እያጠናከረ የሥልጣን እድሜውን ሊያራዝሙለት የሚችሉ መሆናቸውን ከግምት በማስገባት ተገቢው እርምት ማድረጉ ለትግሉ ስኬት ማግኘት ጠቃሚ መሆኑ ቢገለፅም ካፈርኩ አይመልሰኝ በሚል በጀመሩት ቀጥለዋልና በአሁኑ ወቅት ምክር ሰሚ ለመሆናቸው ጥርጣሬያችን እየጎላ የመጣ እንጂ የሚቀንስ አልሆነም።

በበኩላችን ስለምርጫ ስናወጋ በቅድሚያ ግልፅ መሆን ያለበት ዜጎች ነጻነታቸውን የመጎናፀፍ ሁናቴ በአዎንታዊ መልኩ ሊመለስ የሚገባው መሆኑን በጥብቅ እናምናለን። የዚህ እምነታችን መሰረቱ ነፃነቱን ያልተላበሰ ሕዝብ ፍላጎቱን በድምፁ አማካኝነት ሊያስተጋባ የሚቻለው እንዳልሆነ ስለሚታወቅ ነው። ነፃነት ሲባል የሰው ፍጡር ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ የተጎናፀፈው ሰብአዊ ክብሩ ማለት ሲሆን ማንም ይሁን ማ ይህንን ክብሩን ሊገፈው ቀርቶ ሊገድብበት ጨርሶ የማይገባ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ነፃነቱን የተጎናፀፈና ሰብአዊ ክብሩ የተረጋገጠለት ማንኛውም ዜጋ በራሱም ሆነ በሀገሩ የወደፊት እጣ ቢሻው በግለሰብ ደረጃ አለበለዚያም እምነቱን በሚለግሳቸውና የሱ አንደበት ሆነው ሊናገሩለት በሚችሉ ወኪሎች አማካኝነት ተሳታፊና ወሳኝ የመሆን እድሉ የሚረጋገጥለት ይሆናል። ሀገራዊ ኃላፊነት የመሰማት፤ ሀገርን የመውደድና ለሕዝብ ቀናኢ የመሆን መሰረቱም ከዚህ ውጭ ሊሆን እንደማይችልም ደጋግመን የገለፅነው እንደሆነ የሚታወስ ነው።

ስለሆነም ስለ ምርጫ ሲታሰብ በየአራት ወይንም አምስት አመት የድምፅ መስጫ ወረቀትን ከድምፅ ኮሮጆ ከማስገባት በላይ የሚሄድ የዴሞክራሲ እሴት ነው ተብሎም የሚነገረውም በዚሁ የተነሳ ነው። የምርጫ ክንዋኔ በራሱ ዴሞክራሲን የሚያመጣ እንዳልሆነ የሚታወቅ ነው። ነገር ግን አማራጭ የሌለው የዘመናዊ ዴሞክራሲ ሥርአት አካል መሆኑ ግን ምንም ጥርጥር የለውም። ተኣሚነትን፤ እውቅናና ይሁንታን ከሕዝብ የሚያገኝ የምርጫ ትዕይንት ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን፡ መልካም አስተዳደርንና የፖለቲካ ውጥረትን ሰላማዊ በሆነ መልክ ማርገብን ያጠቃልላል ተብሎ አፅንዖት በተሞላበት ሁናቴ እየተገለጸ የሚገኘውም በዚሁ የተነሳ ነው። ይህ ሁናቴ ግን በሀገራችን ለሕዝባችን የውሃ ሽታ እንደሆነ ያለፉት 23 አመታት ከበቂም በበቂ ያሳዩት ናቸው። የምርጫው ህግም አልተስተካከለም፤ የምርጫ ኮሚሽኑም ነጻ ያልሆነና በወያኔ ስር ያለ ነው። ይህ ሳይታረም ወደ ወያኔያዊ ምርጫ መንጎዱ መጨረሻው የተለመደው ውድቀት ብቻ ይሆናል ።

ለዚህም ነው ስለ ምርጫ በሚነገርበት ወቅት ሕዝብ የአገዛዙ አንድ አካልና አምሳል በማለት የሰየመው በአገዛዙ ደጋፊዎች ደግሞ "ከመንግሥት ገለልተኛ የሆነ" ተብሎ የሚሞካሸው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከአምሳሉ ጋር መወገዱ አይቀሬ ነው ተብሎ የሚገለፀው። ሌላው መነሳት ያለበት ከምርጫ እንቅስቃሴ ጋር በጥብቅ የተያያዘው የፕሬስ ነጻነት ጉዳይ ነው። ፕሬስ መሰረታዊ ሚናውን (ማስተማር፤ መቀስቀስ፤ ማደራጀት፤ የውይይት ርዕስ አዘጋጅቶ ማቅረብ) ለመጫወት ይቻለው ዘንዳ ነፃነቱ ተጠብቆና ተከብሮለት ሊንቀሳቀስ ይገባል እንጂ የተለያዩ የመቆጣጠሪያ ሕጎችን እየደነገጉ ፕሬስን ሽባ ማድረግና ጋዜጠኞችንም ማሸማቀቅ የወያኔ ዋና ተግባር በሆነበት ፍትሃዊ የሆነ ሕዝባዊ ምርጫ ሊካሄድ የማይችል መሆኑ ያለፉት ተመክሮዎች የሚያመላክቱት ናቸው።

ለዚህም ነው በኢሕአፓ እምነት ስለ ምርጫ ካወጋን አይቀር በሀገራችን ሊካሄድ የሚገባው ምርጫ ሕዝብ ለአገዛዙ ተውኔት አዳማቂነትና ይሁንታ ለመስጠት የሚገደድበት ሳይሆን ሕዝባዊነትን የተላበሰ በሕዝቡ ፍላጎት ላይ ሊመሰረት የሚችልና ሀሳቡን በነፃ ሊገልጽበት የሚያስችለው፣ ከተለያዩ አማራጮች መካከል ልቡን የሚኮረኩሩለት ጥቅሞቹንና ፍላጎቶቹን የሚያስከብርለትን እይታዎችንና ፕሮግራሞችን ለመምረጥና ለመወሰን የሚያስችለው ሰላማዊና ሁሉንም አሳታፊ ሊሆን የሚችል የፖለቲካ ምህዳር መኖርን ሕዝባችን ይፈልጋል።

ታዲያ ይህ ከሆነ ዘንድ ምን መደረግ አለበት ምንስ ማድረግ ይጠበቅብናል?

በበኩላችን ከሁሉ አስቀድሞ ይህ ይካሄዳል ተብሎ የሚጠበቀውን ተውኔት በመነሻነት በመውሰድ ሕዝብን ይበልጥ በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ ከምንጊዜውም በበለጠ ለመቀስቀሻ፣ ለማደራጃና ለማታገያ በሚያስችል መልክና አንድነቱን በማያፋልስበት ሁናቴ መጠቀሚያ ለማድረግ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑ፣ የሀገር ዳር ድንበሯ እንዲከበርና ሉዓላዊነቷ እንዲረጋገጥ፣ የሕዝቦቿም ችግር በኢትዮጵያ ማዕቀፍና በዴሞክራሲ መንገድ ይፈታል ብለው የሚያምኑ ሀገር ወዳድ ኃይሎች ተፈላልገውና ተጠራርተው መወያየትን የሚያመላክት እንደሆነ ግልፅ ነው። የግንኙነታቸው ጭብጥም ሊሆን የሚችለው በሀገር አድንና ሕዝቧን በመታደግ ዘመቻ ዙሪያ የታጠረ ሊሆን ይገባዋል። በዚህ ላይ ውይይት በማድረግና ከጋራ መግባባት በመድረስ ሃሳባቸውን በጋራ ለሕዝብ ለማስተላለፍ የሚያስችላቸውን መድረክ በጋራ ለመፍጠር ይቻላቸው ዘንዳ በሚቀጥሉት መሰረተ-ሃሳቦች ላይ ከስምምነት መድረስ ተከታዩ እርምጃቸው ይሆናል።

ስለሆነም በዚህ አመት ይደረጋል ተብሎ በሚጠበቀው ምርጫ እየተሽቀዳደሙ ለመሳተፍ ከመሯሯጥና ቅሌትን ከሕዝብ ከመከናነብ በፊት እርጋታንና አርቆ አስተዋይነትን በመላበስ ቀጥተኛ ፤ ነፃ ተሳትፎና ርቱዕ ምርጫ በሀገራችን በተግባር እንዲውል መሰረት ለሆኑት እሴቶች በቅድሚያ እንዲሟሉ በጋራ መንቀሳቀስ አግባብነት ያለው ይሆናል። እነዚህም፡-

- ከሁሉ አስቀድሞ የታሰሩ የፖለቲካ ድርጅት፡ የነፃ ፕሬስ፡ መንግሥታዊ ያልሆኑ የሲቪልና የሙያ ማህበራት መሪዎችና ንቁ አባሎቻቸው ያለምንም ቅደመ ሁናቴ የሚፈቱበት፤
- ነፃ የሆነ የፖለቲካ ምህዳርና ያልተገደበ የዴሞክራሲ ሥርአት ይሰፍን ዘንድ የሕዝብ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን በወረቀት መዘርዘሩ ሳይሆን በተግባር የሚረጋገጡበት፤
- ገለልተኛና በሁሉም ተዋኒያን ተዓማኒነትን የሚያገኝ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ መኖርና አባላቱም የነዚህኑ ስምምነት ያገኑ የመሆናቸው ጉዳይ፡
- ነፃና ገለልተኛ የሆነ የፍርድ ተቋም የሚገነባበት፤
- ሰለ ምርጫው ሕግ ደንብና ሂደት አፈፃፀሙ ተዓማኒነት ማግኘትና ሁሉም ወገን አክብሮ የመገኘቱ ጉዳይ፤
- የምርጫ ሂደቶችና አፈፃፀማቸው ሳንካ እንዳይገጥማቸው የዜጎች ሙሉና ንቁ ተሳትፎ የመኖር፤
- በሕዝብ ኃብት እንዲንቀሳቀሱ የተደረጉ የመገናኛ ብዙሃን ለአገዛዙ የፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ መሆናቸው ቆሞ በእኩል የመጠቀምና ሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ለምርጫ የሚያስፈልጋቸው ወጪን በእኩል የማግኘት መብት መከበር፤

- ተወዳዳሪዎች ከቦታ ቦታ በነጻ ያለአንዳች ተፅዕኖ የመንቀሳቀስ፤ ሕዝብን የመቀስቀስና የማደራጀት እንዲሁም የቅስቀሳ ወረቀቶቻቸውን መፈክሮቻቸውን የማሰራጨት መብት መከበር፤
- ለምርጫው ሂደት ጉድለት ላለመኖር እድሉ የሰፋ እንዲሆን በተወዳዳሪዎቹ ተዓማኒነትን ሊያገኙ የሚችሉ ሀገር በቀል የገለልተኛ ታዛቢዎች መኖር፤
- ነፃ ጋዜጠኞችና የመገናኛ ብዙሃን የምርጫውን ሂደት በአንክሮ እየተከታተሉ ለሕዝብ እንዲዘግቡ ሁኔታው እንዲመቻችላቸው ብቻ ሳይሆን የነፃ ፕሬስ አባላቱም ይህንን ከባድ ኃላፊነት ለመወጣት ድፍረቱንና ከሁሉም በላይ ሚዛናዊነት የሚጠበቅባቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ተቋማት ለአገዛዙ የምርጫ ሂደት መጠቀሚያ መሆናቸው መቆም፤
- ሕዝባዊ ድርጅቶች ለአገዛዙ ተቀጥያ መዳረጋቸው እንዲቆምና በነፃ በመደራጀት ተጠያቂነታቸው ለአባሎቻቸው ብቻ መሆኑን በተግባር መረጋገጥ፤

በተሰኙት ዙሪያ ሕዝብን ለማስተባበሪያ፡ ለማታገያ መጠቀሚያ ማድረግ የወቅቱ ተግባር ሊሆን ይገባል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት መሠረታዊ ሀሳቦች ቀደም ተብሎ የተጠየቁ ቢሆንም ወቅታዊነታቸውና አንገብጋቢነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጡ ከመሆናቸውም በላይ ሃሳቦቹ የድርጅቶች ብቻ ሳይሆን የሕዝቡም ናቸውና ሕዝብን በነዚህ ርዕሶች ዙሪያ ለመቀስቀስና ለማታገል ወሳኝና ቆራጥ አመራር በመስጠት በይፋም ሆነ በሕቡዕ መንቀሳቀስ የግድ ይላል።

ስለሆነም በወያኔ የበላይነት ለሚካሄደውና ለሕዝባችን ምንም አይነት ጠቀሜታ እንደማያመጣ በተረጋገጠው ምርጫ በምንም አይነት ተሳታፊ አለመሆንና ሊመጣ የሚችለውን አደጋ በጋራ ለመቋቋም መዘጋጀቱ የግድ እንደሚል ከግልፅም ግልፅ ነውና በዚህ በኩል ምንም አይነት ብዥታ ሊኖር አይገባም። ተቃዋሚ ድርጅቶች የሕዝቡን ትግል ማስተባበርና ጠንካራ አርቆ አሳቢ አመራር ለመስጠት የሚፈተኑበት ወቅት ላይ የተደረሰ መሆኑ ሁሉም ሊገነዘበው የሚገባ ጉዳይ ነው። መዝረክረክ የሌለበት፤ ውስጣዊ ሚስጥሩን ጠብቆና መስዋዕት ለመክፈል ቆርጦ የተዘጋጀ አመራር ሰጪ ተቋም መኖር ለትግሉ ስኬታማ መሆን የመጀመሪያ እርምጃና ወሳኝነት ያለውም ነው።

ሰላማዊ መሆን ለወያኔ ሕገ አገዛዝ መንበርከክ ሳይሆን የሕዝብ መብት እንዲከበር ማመጽ፣ እምቢኝ አሻፈረኝ ማለት ነው። ከወያኔ ጋር ሰላምና ዕርቅ እንዲኖር መስበክ ትግልን ጎጂ ለመሆኑ ያለፉት 23 ዓመታት ያረጋገጡት ሐቅ ነውና በዚህ ጎዳና አሁንም መሰማራት የሚፈልጉትን ከወዲሁ ማራቅና ወግዱ ማለትም የሚጠበቅ ነው። የተጠቀሱት ሃሳቦች ከሕዝቡ ጋር በመሆኑ እንዲሟሉ መታገል የወቅቱ ግዳጅ ሲሆን ወያኔ በእምቢተኝነት አሻፈረኝ ብሎ ከተፈጠመ (መሆኑ ደግሞ አይቀርምና) ትግሉን አንድ ደረጃ ከፍ ለማድረግ በቅጡ በተቀናጀና በተከታታይ የተቃውሞ እንቅስቃሴን ማካሄድ ቀጣዩን እርምጃ ከወዲሁ ማሰላሰልም የሚጠበቅ ነው። በዚህ ወቅት ሊመጣ የሚችለውን አደጋ በጋራ ለመቋቋም መዘጋጀትም የማይሸሹት ግን የምንቋቋመውም እንደሆነ መረሳት የሌለበት ነው።

በኛ እምነት እነዚህን መሠረተ ሃሳቦች ማንም ለሕዝብ ቅን አሳቢ የሆነ ሀገር ወዳድ በደስታ የሚቀበላቸውና ሊስማማባቸው እንደሚችል እርግጠኞች ነን። የሕዝቡም ጥያቄዎች ናቸውና። ስለሆነም የወያኔን አገዛዝ በማስወገድ ላይ ግልፅ አቋም ያላቸው ድርጅቶች በሀገርና በባዕድ አገር መኖራቸው፣ ምናልባትም በትግል ሥልት የተለየ አመለካከት ሊኖራቸው መቻሉ፣

ጥንካሬያቸውና የአባላት ብዛታቸው መለያየቱ፣ በጋራ እንዳይሰሩ እንቅፋት ሊሆንባቸው አይችልም። አይገባምም። ዋናው ቁምነገርና ትኩረት መሰጠት የሚገባው ወያኔን ቆርጦ ከመታገሉ ላይ እንደሆነ ነው። መረዳዳቱ በርግጠኝነት ከልብ ከተፈለገ ደግሞ ተገናኝቶ ለመወያየት የሚከብድ አይሆንም።

በጋራ መታገሉ ቀርቶ ራሱ ለዚህ ጥሪ መቅረቡና ከስምምነት የመድረስ ፍላጎቱ አይሎ መውጣቱ ወያኔን የሚያስደነግጠው መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነውና የተለያዩ አሰቃቂ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችል ይሆናል። በዜጎች ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋዎችን ሊያደርስ የሚጥር መሆኑም የሚጠበቅ ነው። የተለያዩ ማስፈራሪያዎች እስከ ሀገር ትፈራርሳለች የሚል አስደንጋጭ ዜናዎችንም ሊያሰራጭ ይችላል። ድርጅቶችን ሕጋዊነት ነፍጎ መሪዎቻቸውንና ንቁ አባሎቻቸውን ለእስርና ለሌላ ከፍተኛ ጉዳቶች ለመዳረግ መቃጣቱም የሚጠበቅ ነው። በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችም በመደለል ተቀናቃኞቹን ለመከፋፈል ጥረት ማድረጉም የሚታሰብ ነው። ይህ እስካሁንም ድረስ ተግባራዊ በመሆን ላይ ያለ ስለሆነ ማንንም ሊያሸማቅቅ አይገባውም። ተወደደም ተጠላም ነፃነትን የመሰለ ክቡር እሴት በልመናና በፀሎት ተገኝቶ አይታወቅምና የጭራቅ ማስፈራሪያ ሊያደርጉ የሚጥሩ ከፋፋዮችን ከወዲሁ ነቅቶ መጠበቅና የመከላከያ ዘዴን ማዘጋጀቱ ከተቃዋሚ ድርጅቶች የሚጠበቅ እንደሆነም የምንዘነጋው አይሆንም። በመሆኑም ይህንን አመት ሕዝብን በጋራ አቋምና በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ በማስተባበር ወያኔን በሁለገብ ትግል ከሥልጣን ለማስወገድ በጋራ እንድንጠቀምበት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። ከዚህ የበለጠ አኩሪ ድርጊት የለምና። ስለሆነም ከምርጫ በፊት ነፃነትን ብንጎናፀፍ አይበጅም?!

ነፃነትን ለተላበሰ ሕዝባዊ ምርጫ በጋራ እንንቀሳቀስ!

ወያኔ በጋራ ሕዝባዊ ትግል ይወገዳል!